# ሃምሳ አለቃ ደሳለኝ

ከቴድሮስ ሀይለ tadyha@gmail.com

ከደርጉ የገበሬ ማሕበር ካድሬዎች በገራገርነቱ የሚታወቀው የጎጃሙ ቆምጫምባው እንደዋዛ አለ ተብሎ ከሚነገርለት አባባል አንዱ ጋዜጠኛ ለመሆኑ ከቡርነቶ የአሜሪካንን ኢምፔሪያሊዝም እንዴት ይመለከቱታል ሲል ለጠየቃቸው ጓድነታቸው ሲመልሱም ባልተንዛዛ አማርኛ የጎሪጥ ነው የማየው ሲሉ ቆፍጠን ያለ መልስ እንደሰጡ በቀልድ መልክ ሲነገርና ለአንዳንድ ግልገል ካድሬዎችና አድርባዮችም ጭፍን አቋምና ባዶ ፕሮፓጋንዳ እንደ ምሳሌ ሲቀርብ ይስተዋላል፤፤

ከጭፍን ካድሬዎችና ከእበላ ባይ ጭፍሮች ያልተላቀቀው የሃገራችን ፖለቲካ ይትባህል ዛሬም ከትላንቱ በባሱ የፖለቲካ ደናቁርትና ምንደኞች ሳይላቀቅ ሦስት አሥዕርተ አመታት አልፈውታል ታዲያም ከትላንት የዋሀ የለብለብ ካድሬዎች የዛሬዎቹ ሲነፃፀሩ አንዳንድ ገራገሮች ባይጠፉም በአብዛኛው ግን እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል አለች እንደተባለው እንስሳ ሆዳቸውን ያስቀደሙና አይናቸውን በጨው አጥበው በድርቅና ጥፋት መሆኑን አውቀው ለጥቅም የተሰማሩ የአባትህ ቤት ሲዘርፍ አብረህ ዝረፍ የሚለውን ሠይጣናዊ ጥቅስ መመሪያ በማድረግ የሀገር ውድቀት የህዝብ ጉስቁልና ዋይታና ሰቆቃ አይተው እንዳላዩ በመምሰል በወገናቸው ላይ ለሚፈፀመው ኢ ፍትሐዊ ተግባር ተባባሪ በመሆን የተሰማሩ ካድሬዎችና ለዚህ የግፍ ተግባር ለመሰማራት የሚቋምጡ ጭፍሮች በሃገርም በውጭው ዓለምም እየተበራከቱ በመሄድ ላይ ናቸው ፤፤

ከምንም በላይ አሳዛኝ የሚሆነው የተማረው ክፍልና የሰው ልጅ መብትና እኩልነት በተረጋገጠበት ሁሉም ሰው ከህግ በታች በሆነበት እንኳን ለዜጋው ለኛ ለስደተኞቹም የተትረፈረፈ የመኖር ፣ የመስራትና ፣ የመከበር እድል ባለበት ሃገር እየኖረ የዲሞክራሲ ፣ የእኩልነትና ፣ የህግ የበላይነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ እየኖረው እያየው ያለ ወገን በዘረኝነት ፣ በአንባገነንነት ፣ በወንጀለኛለት በተጨማለቀው የመለስ አስተዳደር መከራ ፀንቶበት ያለው ህዝባችን ከዚህ ከተጫነበት የግፍ ቀንበር ከላዩ ወርዶ በእኩልነትና በነፃነት የሚኖርበትን ግዜ በመናፈቅ ላይ ባለበት በዚህ የመከራ ወቅት ለግዜያዊ ጥቅምና ለማይጨበጠው የወያኔ ማባበያ የተስፋ ቃል ታምኖ ለግፈኛው ስርአት ለማደግደግ የሚያኮበክበው ጥቅመኛና ተንበርካኪ የሆዳም መንጋ አሳፋሪ እንቅስቃሴ ከመቼውም ግዜ

በላይ በተለይ በሰሜን አሜሪካ እየተስፋፋ የመጣ እንደሆነ የሚጠቁም ሁኔታዎች እየተስተዋለ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በያቅጣጫው ነቅተን እንድንገኝና ለዚህ አሳፋሪና ርካሽ ተግባር የረከሱትን ወገኖቻችንን ልናነቃና ከዚህም ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ልንመክራቸው መቃብሩ ከተማሰው ካረጀና ካፈጀው የመለስ አገዛዝ ጋር ባለቀ ሰዓት ከመነካካትና ለዘርማንዘር ከሚተርፍም ወራዳ ታሪክ እንዲድኑ ልንመክር የሚገባ ይመስለኛል፤፤

የመለስ ዜናዊ ሽብርተኛና ወንጀለኛና አገዛዝ በየጊዜው ማንነቱ እየተጋለጠና ሠይጣናዊነቱም እየተረጋገጠ በመጣበት በአሁን ጊዜ በተለይም ለዚህ ለዛሬው ለመለስና ለጀሌዎቹ እዚህ መድረስ እልፍ አእላፍ ልጆቹን የገበረው ለረጅም ዘመናት የጦር አውድማ በመሆን የሰቆቃ ሕይወት የገፋው የትግራይ ህዝብ ከመቼውም ግዜ በላይ የነመለስን አጥፊነት ተገንዝቦ ከኢትዮጵያዊው ወገኑ በዘረኝነት ለይተው ለስልጣናቸው ማርዘሚያ ከሌላው ብሔር ጋር በማናከስ ማቆሚያ በሌለው የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ተወጥሮ የኖረው የትግራይ ወገናችን በአሁኑ ወቅት አሠላለፉን አስተካክሎ እብኝ ለኢትዮጵያዊነቴ ብሎ በሃገርም በውጭም ሃገር ያለው ዜጋ እያሳየ ያለው የትግል መንፈስ ያደናገጠው የመለስ ቡድን በትግራውያን ያጣውን ድጋፍ ለማካካስ በተለይ የአማራ ተወላጆችን በጥቅማ ጥቅም በመደለል ጭፍራ ለማሰባሰብ ሠፊ ዘመቻ ከጀመረ ሰነባብቷል ፤፤

በተለይ እራሱን ብአዴን ብሎ የሚጠራው አንዳንዶች እንደሚሉት የሕወሐት የአማርኛ ዲፓርትመንት ባለፈው ሰሞን ካድሬዎችን ወደ ሰሜን አሜሪካ ልኮ ስለ ልማትና ዲሞክራሲ ለመስበክ ሙከራ አድርጓል ከዚህ ቡድን የተልኮ አላማዎች ዋንኞቹ ቢቻል የአማራውን ተወላጆች ከክልል በማውረድ ለቁጥጥር እንዲመች ወደ አውራጃና ወረዳዎች ዝቅ አድርጎ በማደራጀት መሰሪ የፖለቲካ ተግባሩን ለማራመድ ሲሆን በተለይ የጎጃም ልማት በሚል ባደረገው የተናጥል ስብሰባ ሙከራ ብዙሀኑ ሴራውን በመረዳት ተቃውሞውን ገልጾ ራሱን ያገለለ ቢሆንም በጣት የሚቆጠሩ  የጎጃም ተወላጅ ኢትዮጵያውያንን ላይ ግን መርዙን ረጭቶ መሄዱን ለመታዘብ ተችሏል ፤፤

አበው "ጃንደረባ ሎሌ በጌታው ብልት ይፎክራል" እንዲሉ መቀመጫውን ባሕር ዳር ያደረገው የወያኔው ተለላኪ ብአዴን በአማራው ሕዝብ ላይ የፈፀመውና ያስፈፀመው ሠቆቃ ከቶ የሚረሳ መሰለው እንዴ እነ ታምራት ላይኔ እንዲህ እንደ ሸንኮራ ተመጦ ሊተፋ ያኔ ወደ ሱማሌውና

ወደ አፋሩ ሄደው ሽርጣም ይልሃል ጊዜው ያንተ ነው በለው እያሉ ስንቱን ኢትዮጵያዊ በጎሳው ምክንያት አስገደሉ የተፈናቀለውና መድረሻ ያጣውና የትም ተበትኖ የቀረውን ዜጋ ቤቱ ይቁጠረው ያኔ ታድያ ነብሳቸው ይማርና የዘጠና አመት አረጋዊ አያቴ ወያኔ ሕዝባችን ላይ ያወረደውን መዐት ታዝበው እንዲህ ሲሉ ስንኝ ቋጥረው ነበር "ጣልያን ምን አጠፋ በከንቱ ኩነኔ፣ ሀገሩን አጠፋት መለስ እና ላይኔ፤፤ ለመለሰ ሙክት ለያይኔ ወጠጤ፣ ይህን ሠጥቼ ነው በሀገር መቀመጤ፤፤" ብለው ነበረ በተለይ በአማራው ክልል ብቻ ተለይቶ የተካሃደው እጅግ በቀለኛ በሆነ መልኩ የተከናወነው የመሬት ድልድል ብዙዎችን ወልደው ከከበዱበትና እትብታቸው ከተቀበረበት አጽመ ርስታቸው በማፈናቀል ለከፋ ድህነትና ስደት በመዳረግ በሕወሀት ትዕዛዝ በብአዴን አሸከርነት የተከናወነው የግፍ ተግባር በቅርብ የምናስታውሰው ነው፤፤

ሌላም ከዚሁ ከገበሬው አካባቢ ሳንወጣ በደርግ ዘመን ከተቋቋሙት የገበሬ ማሕበራት ውስጥ በሞዴልነት ይጠቀስ የነበረው በጎጃም ክፍለ ሐገር በቢቸና አውራጃ የሚገኘው የየትኖራ የገበሬ ማሕበር ከዚያ በፊትም ያልነበረ ከዚያ በኋላም ያልታየ ጠንካራና ትልቅ እመርታ ላይ ደርሶ የነበረ ከኋላቀሩ እርሻ ወጣ በሎ በትራክተርና በኮምባይነር የማምረት ደረጃ የደረሰ ፤ እያንዳንዱ የገበሬ ቤት በቆርቆሮ የሰራ አረጋውያን የሚጦሩበት ህፃናት የሚማሩበት መዋቅር የዘረጋ ፤ ከፍተኛ ምርት ለማስመዝመገብ የቻለና ሰፊ የደን ልማት ፤ ደረጃውን የጠበቀ የእንግዶች ማረፊያ ሆቴል ዘመናዊ የከብትና የንብ እርባታ የነበረው ያን የመሰለ የገበሬዎች ተቋም ወያኔ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ የማሕበሩን መሪዎች በማሰር የተቋሙን ንብረት በመዝረፍ እና ደኑን በመመንጠር በወሰደው የበቀል ድርጊት የአካባቢውን ተወላጆች ወደ ከፋ ድህነት ዳግም እንዲመለሱ በማድረግ የፈፀመውን ግፍ ድፍን ጎጃም የሚያውቀው ቢሆንም የገዛ ወገናቸውን ደም መጣጭ በመሆን የፋፉት እንደ አያሌው ጎበዜ አዲሱ ለገሰ ያሉ የበአዴን ጃንደረቦች በተቆጣጣሪያቸው በበረከት ስምዖንና እንደ ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ባሉ ያለ ብሔራቸው በምደባ በተቀመጡ ጭቃ ሹሞች መሪነት የተካሄደውና አሁንም ባልተገታው የበቀልና የጭቆና አገዛዝ ሕዝባችን የሚገፋው የሰቆቃ ሕይወት መቋጫ አላገኘም ፤፤

እንዲህ አይነት የገለማና እንደመርገም ጨርቅ የበከተ ታሪክ ያለው ብአዴን እናት ድረጅቱን ኢሕፓን ከማስደምሰስ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ወያኔን በቅን አገልጋይነት አሰስ ገሰሱን በመሸከም የጭነት ተግባሩን በመወጣት ላይ ያለ የአጠቃላይ ድርጅቱ ሕልውና ከሕወሐት ክፍፍል በኋላ ከቡድን

ንብረትነት ወደ ግለሰብ ወደ መለስ የግል እቃነት ያለ አዋጅ የተወረሰ እንኳን አሁን ለሚመለምላቸው ግልገል ካድሬዎችና ጥቅመኛ ጭፍሮች አይደለም ለነባር አባላቱም የኔ የሚሉት እጅና እግር ያለው አቋም የሌላቸው በሕወሐት መለስ ሳንባ የሚተነፍሱ ሰው መሰል ሰዎች የበዙበት ተቋም ሆነው ሳሉ ህዝቡ ሌላ አማራጭ እንዳይኖረው ቀን ከሌት በተለያዩ ሁኔታዎች በመወጠር ተቃዋሚ ተብሎ በሚፈረጀው ላይ በማስፈራራት በማሰርና በመግደል የከፋ ጨካኝ የክልል አስተዳደር በመሆን በጌታው ዘንድ ታማኝነቱን ለማስመስከር ዘወትር የማይፈጽመው ወንጀል የሌለው ተቋም ነው ፤፤

እንዲህ የአማራውም ሆነ የመላው ኢትዮጵያዊው ዜጋ እድልና መብቱን በነጻነት የመምረጥ እድል እንዳይኖረው እስከ ጎጥና ቤተሰብ የወረደው የወያኔ የአፈና መዋቅር ተቀፍድዶ የሚያርሰውን መሬትና ከውጭ በእርጥባን የመጣን የእርዳታ እህል እንኳ ለማግኘት ወያኔንና ጭፍሮቹን መምረጥ እንደግዴታ ተጥሎበት በከባድ የአገዛዝ ቀንበር ስር እንዲማቅቅ የተደረገው ወገናችን ከዚህ እስከፊ አገዛዝ ነጻ እንዲወጣ የበኩሉን ጥረት ማድረግ የሚጠበቅበት በምዕራቡ ዓለም ያለው ዜጋ ብዙ የዲፕሎማሲ የገንዘብና የፖለቲካ እገዛ የሚያደርጉ አያሌ የወገን ኩራት የሆኑ ወገኖች የመኖራቸውን ያህል "የእሳት ልጅ አመድ እንዲሉ" ለቁራሽ መሬትና ለጥቅማጥቅም የተገዙ እጅግ በጣም ጥቂት የሆኑ ግለሰቦች ያውም አንዳንዶቹ የዚያ በባርነት እገረ ሙቅ እጅ ከወርች የታሰረው ገበሬ ቤተሰብ የሆኑ ይህን ግፍና መከራ እንዳላዩ ሆነው (ለደም መሬት) ሱሪያቸውን ዝቅ ላደረጉት አደግዳጊ የጠላት አሽከሮች ምክርና ተግሳጽ ይገባቸዋል፤፤

በዚህ በሰሜን አሜሪካ ያሉ ጥቁር አሜሪካዊ ወንድሞቻችን ለዘመናት ተጭኖአቸው የኖረውን የባርነት ቀንበር በመራራ ትግላቸው ሰባብረው ዛሬ የነሱ ትግል ውጤት ያመጣው ነጻነትና ፍትሕ ተጠቃሚ በመሆን ከጨካኙ የወያኔ ሕገ አረዊት አገዛዝ አምልጠን በሰላመና በነጻነት እየኖርን ያለነው በሺህዎች የምንቆጠር ኢትዮጵያውያን ለፕሬዘደንት ኦባማ የምርጫ ዘመቻ በብዙ መልኩ ያሳየነው ተሳትፎ የሚታወስ ሲሆን ከሂደቱም ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ውጤቱ ጣፋጭ ሂደቱም ስልጡን መሆኑን ለማየት ችለናል ፤፤ የሰው ልጅ መሪውን በነጻነት የመምረጥ መብት የድሎች ሁሉ መሰረት በዚህ ዘመን በየትም ያለ ሰብአዊ ፍጡር ሊያገኘው የሚገባ ፀጋ ሆኖ ሳለ ምስኪኑ የኛ ወገን ግን ጊዜ በሻረው የስብስቴ ዘመን ኋላ ቀር ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስር ወድቆ በአንድ መናኛ ግለሰብ እጅና እግር በሌለው የተምታታ ርዕዮትና የማንነት ቀውስ በፈጠረው የተሳከረ ትንተና በዘርና በጎጥ በጭቃ ሹምና

በምርኮኛ እላያችን ላይ ጭኖ የምናዳምጠውን አይደለም የምናስበውን ለመቆጣጠር የድርጅት መዋቅሩ እጓዳችን ድረስ ዘርግቶ የማያላውስና ሃገሪቱን ሠፊ እስር ቤት ያደረገው የወያኔው ቡድን ቁመትና ወርዱን ለዛና መአዛውን ጨርሶ በማያውቀው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አሸነፍኩ የሚል ነጠላ ዜማ ማንጎራጎር ጀምሮአል፤፤

እነ አቶ መለስ ምርጫ ባሉት ቅርጫ መሡል ባዶ የቧልት መድረካቸው ለወትሮው እንኳን ለአጫፋሪነትና ለጨለምተኛ ዲሞክራሲያቸው መጀቦኛነት ከቀንድና ከጭራው ይቋደሳሉ ብለን የገመትናቸው ታማኞቹ ተቃዋሚዎች ጥቂት ወንበር በመስጠት ለምዕራቡ እርዳታ መለመኛነት ይጠቀም የነበረበትን ተውኔት ወደ ጎን አድርጎ ያለ አንዳች ሃፍረት 99% አሸናፊ እንደሆነ ያወጀበት ሰይጠናዊ ምርጫ ለአብዛኞቻችን አስቀድሞ ውጤቱ የታወቀ ቢሆንም በዚህ ጠባብ ቀዳዳ በመጠቀም ለትግሉ ጠቃሚ ውጤት ለማስገኘት ለጣሩት ወገኖች ያለኝን አድናቆት በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ ሰላማዊ ትግሉ ገና አልተጀመረም ብለው የሚባጁት ወገኖችም ሰይፍና ጎመድ ይዞ እያደባ በማታለል በምርጫ ስም ነጣጥሎ ከሚመታቸው ከሕገ አራዊት አገዛዝ በእርግጠኝነት ለመናግር እርማቸውን ያወጡ ይመስለኛል  የዚህ ድራማ ተውኔት ተጠናቆ መጋረጃው በመገለጡም ለሌላ ተመሳሳይ ድራማ ለሚቀጥለው አምስት አመት ሰልፍ ይዞ የሚጠብቅ የዋህ ካለ ጊዜ ጉልበት ሐብትና እድሜ ማቃጠል መሆኑን መምከር ይገባል፤፤

ወደ ርዕሳችን እንመለስና “ሐምሳ አለቃ ደሳለኝ” ማን ነው ትሉ ይሆናል የዛሬው የሃገራችን ሽክምና ችግር የሆነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ያኔ በትግሉ ዘመን ለስንቅና ትጥቅ ማመላለሻነት ይጠቀምበት የነበረ የረጅም ጊዜ አገልግሎት እንደ ሰጠ የተነገረለት አህያ የተሰጠው ስምና ማዕረግ ሲሆን የሚጠሉና የሚፈሩትን እነሱ የደርግ የሚሉት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አካላትን ለማዋረድ ወያኔዎች አጋሰሳቸውን “ሐምሳ አለቃ ደሳለኝ” ብለው እንደነበር ያኔ በድሉ ዋዜማ እብሪት ባዶለደመው ብእራቸው በእፎይታ መጽሔት ታሪክ ብለው ከጫሩት የተወሰደ ነው ፤፤ በእርግጥም ላለፉት የወያኔው የአገዛዝ ዘመን እስከአሁንም ድረስ እንደ አጋሰስ የሚፈረጅ ሕብረተሰብ ባይኖርም በዚህ ሽብርተኛ ቡድን ዙሪያ ተኮልኩለው ሕዝብን ለመርገጥና የጭቆና ዘመኑን ለማርዘም በውሸትና በማስመሰል ለወያኔ በማገልገል ላይ የሚገኙት ብአዴን ኦህዴድ ደህዴግ እና ሌሎችም ራሳቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም አስገዝተው እንድ ሐምሳ አለቃ ደሳለኝ አሰስ ገሰሱን በመሸከምና በመላላክ ለተጠመዱ

ሆድአደር ጥቅመኞች እንደሰው ተፈጥረው እንደ እንስሳዋ ለሆኑት ይበልጥ ስያሜው ይስማማል እላለሁ፤፤